ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፤
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዚአብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

**ቁጥር ፲፩/፳፻፫ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ
ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥
ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡
ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ
ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እግዚአብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥
እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና
ካህናችን፥ ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡
በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

# ይድረስ፡-

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥
በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥
በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥

ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና
በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡
"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥

በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!

እንዲሁም፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

እንዳለፈው፡ እንደ፲፩ኛውና ከእርሱ እንደቀደሙት ተከታታይ መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎቼ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዚአብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ**።

## መቅድም

ለዚህ፡ ለዛሬው የዐዋጅ ቃሌ መገለጥ አስፈላጊነት፡ መነሻ የኾነውን ምክንያት፡ አስቀድሜ ልገልጥላችሁ! እርሱም፡ በቅዱሱ ኪዳን ያገኘኋችሁ፡ እናንተ፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት፡ የቃል ኪዳን ልጆቼ ናችሁ። እናንተን በሚመለከት፡ በእኛ ዘንድ ያለውን ዐሳብ፡ ለፍጥረታተ-ዓላማችን አሳውቃለሁ።

## የ"ኢትዮጵያ ልጆች" ለመባል ያበቃው ሙያ፡ ምንድር ነው?

ጥንቱኑ፡ ከመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን የፍጥረት ልደት ጊዜ፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!"፥ ከዚያ ተከትሎም፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር እም መንግሥትነት መከሠት ጊዜ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" ተብላችሁ፡ በቀደሙት ምዝላቶቻችሁ አማካይነት፡ ሕያዋን ኾናችሁ የኖራችሁት፡ እናንተ የዛሬዎቹ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ናችሁ።

ይህን እግዚአብሔራዊ እውነታም፡ ከዘመነ አዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚያሰኘው ስያሜ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" በሚለው የተተካ መኾኑን፡ "'<u>አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!</u>' ይቤ **እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።"**

"ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ <u>‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።›</u> አለ።" የሚለው፡ ቀድሞ፡ በነቢያችን በአሞፅ አፍ ያናገርነው ቃል፡ አረጋግጦ ይመሰክርላችኋል። (አሞ. ፱፥ ፯።)

እናንተ፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ልጆቼ፡ በዚህ ዓለም፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ ከኖረውና እየኖረ ካለው የሰው ዘር መካከል፡ እየራሳችሁን ለይታችሁ፡ ለዚህ ኪዳናዊ ምንነታችሁና ማንነታችሁ ለማብቃት የቻላችሁት፡ እኛ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር፡ ከሌላው ፍጡራችን ኹሉ ይልቅ፡ ለእናንተ ብቻ፡ አድልተን፡ ያደረግንላችሁ፡ ልዩ ነገር፥ ወይም፡ የሰጠናችሁ፡ ልዩ ስጦታ ኖሮ አይደለም።

ነገር ግን፡ ከሌላው የፍጥረት ወገን ኹሉ ይልቅ፡ ከመላእክቶቻችን እንኳ ሳይቀር፡ አብልጠን፡ ለሰብአዊው ፍጡራችን ኹሉ፡ ለእያንዳንዱ ወንድ እና ለእያንዳንዷ ሴት፡ ያደረግነው፡ ልዩ ነገር፥ ወይም፡ የሰጠነው፡ ልዩ ስጦታ በኾነው፣ ከእኛ፡ በተፈጥሮ ባኅናጸፍናችሁ መልካችን ብቻ ሳይኾን፡ "ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር አብወእም፥ ከእግዚአብሔር ወልድ እና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ እንደአንዳችን እንድትኾኑ፡ ያበቃችሁ ዘንድ፡ <u>በዚያው፡ በተፈጥሮአዊው ሥርዓት፡ በለገሥናችሁ መለኮታዊ ጸጋ ለመጠቀም፡ ፈቃደኞች በመኾናችሁ ጭምር ነው።</u>

ያም መለኮታዊ ጸጋ፡ ሕይወትን፥ ወይም፡ ሞትን የሚያስከትለውን፡ ማናቸውንም ዓይነት፡ የፈለጋችሁትንና የወደዳችሁትን፡ ቀናውን ኾነ፡ ጠማማውን፥ እውነቱን ኾነ ሓሳቱን፥ ደጉን ኾነ ክፉዉን፥ ጠቃሚውን ኾነ፡ ጎጂዉን ዐሳብ፡ ለማሰብ እና/ወይም፡ ቃልን፡ ለመናገር፥ በተለያየ ሙያም፡ ስሜትን፡ ለመግለጽ እና/ወይም፡ በተግባርም ለመፈጸም ትችሉ ዘንድ፡ ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡራችን፥ መናፍስት ለኾኑት፡ ለመላእክታቱ ሳይቀር፡ ያቀዳጀነው፡ <u>የመፈለጉ መብትና የመምረጡ ነጻነት፥ የመወሰኑ ሥልጣንና፥ የማድረጉ ኃይል</u> መኾኑን ታውቃላችሁ።

## የኢትዮጵያ ልጆች ኾናችሁ፡<br>ምን አደረጋችሁ?

፩ኛ፡ <u>በዚች ምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ ከኖረውና እየኖረ ካለው፡ ከሰው ዘር መካከል፡ በዚህ መብቱና ነጻነቱ፥ በዚህ ሥልጣኑና ኃይሉ፡ በእውነትና በርትዕ [በትክክል] በመጠቀም፡</u> እስካኹንና አኹንም፡ ከግዙፉም፥ ከሥውሩም፥ ከሥጋዊዉም፥ ከመንፈሳዊዉም ተቃዋሚ ባለጋራ፡ ማንንም ሳይፈራና ሳያፍር፥ በአጥፊው ክፉ ወገን በሚቀርብለት የሽንገላ ጥቅምም ሳይደለልና ሳይማረክ፥ ሳይታለልና ሳይሸነፍ፡ ሳይገበዝና ይሉኝታ ሳይኖረው፡ ከአዳም እና ከሔዋን ጀምሮ፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ባገኘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቱና ምግባሩ ሳይወላውል፡ እስከመጨረሻው በመጽናት፡ እኛን ፈጣሪውንና የእኛ የኾነውን ኹሉ፡ በፍጹም ታማኝነትና ቆራጥነት፡ ፈልጎና መርጦ፥ አምኖና ተቀብሎ፡ በተግባር ላይ ለማዋልና ለፍሬ ለማብቃት የቻለ ማነው? እናንተ ብቻ አይደላችሁምን? ሌላማ የታለ! አዎን! እናንተ ብቻ ናችሁ።

፪ኛ. ለሰው ልጆች ኹሉ የሰጠናቸው፡ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፣ እነርሱም፡-

፩. በጋብቻ ምልክትነትና ማኅተምነት፡ ለአዳምና ሔዋን፥

፪. በቀስተ ደመና ምልክትነትና ማኅተምነት፡ ለኖኅ፥

፫. በሕዝባዊ፥ ክህነታዊና መንግሥታዊ የኅብስትና ጽዋ የቍርባን ምልክትነትና ማኅተምነት፡ ለመልከ ጼዴቅ፥

፬. በግርዛት ምልክትነትና ማኅተምነት፡ ለአብርሃም፥

፭. በጽላትና በታቦት ምልክትነትና ማኅተምነት፡ ለሙሴ፥

፮. በዘውዳዊ ዙፋን ምልክትነትና ማኅተምነት፡ ለዳዊት የተሰጡት፥ በመጨረሻም፡

፯. በሥጋና በደም የቅዱስ ቍርባን ምልክትነትና ማኅተምነት፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተገኘው ኪዳን ምሕረት፡ እነዚህን ኹሉ ኪዳናት፡ የእስራኤል የተባሉት፡ የኋለኞቹ አራቱ ጭምር፡ ወደኢትዮጵያ፣ ወደልጆቼ መጥተውና እስከአኹኗ አፍታ ድረስ፡ በባለቤትነት እና በባለአደራነት ተጠብቀው የኖሩት፡ በእነማን ነው? በእናንተ በቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን ብቻ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

"እስራኤል ነን!" በሚሉት፡ በአይሁድም ኾነ፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ወገን፥ በሌላውም፡ በየትኛውም፡ የዓለም ሕዝብ ዘንድማ፡ ይህ ኹሉ፡ የት አለ? አዎን! የለም።

፫ኛ፡ ልጄን ወዳጄን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ "ክርስቶስ" ብለው፡ እየራሳቸውንም፡ በእርሱ ስም፡ "ክርስቲያን!" ብለው የሚጠሩት የዓለም ሕዝብ ወገኖች፡ እኔን፡ በአንዱ አንደበታቸው፡ "እመ-እግዚአብሔር ጸባዖት! የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት!" እያሉኝ፥ በሌላው አፋቸው ደግሞ፡ "ከፈጣሪ በታች፥ ከፍጡራን በላይ ናት!" በማለት፡ እውነተኛ ማንነቴን፡ እንዲህ በእየራሳቸው ክደው፥ ለሌላውም እያስተማሩ፡ በሚያማስኑበት ጊዜ፥ ለጾታ መሰል ሴቶች ልጆቼም፡ በተፈጥሮ የሰጠናቸውን፡ መለኮታዊዉን ጸጋና ክብር፡ ፈጽመው ነሥተዋቸው፡ እንዲህ፡ እያዋረዱ በሚያጎሣቍሏቸው ጊዜ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽራው ልኾንና በእኩያነት ዐብሬው ልኖር፥ ልጃችንን እግዚአብሔር ወልድንም ልወልድለት፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም፡ በተዋሕዶ አንድነታችን ላሠርፅለት፡ ጾታ ካልነበረው፡ ከእግዚአብሔር አንድነቱ፡ በተባዕትነት [በወንድነት] ጾታ ከተከፈለው፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋራ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም ኾኜ፡ በእንስትነት [በሴትነት] ጾታ የመከፈሌን እውነታ፡ ገሃድ አውጥተው፡ ለመላው ዓለም ያሳወቁ፡ እነማን ናቸው? በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችን የኾናችሁት፡ እናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ አይደላችሁምን? አዎን! እናንተ እኮ ብቻ ናችሁ! ሌላማ፡ ማን አለ? ማንም የለም።

፬ኛ፡ የእኔን የእግዚአብሔር እም፡ ጽላተ ኪዳንነትና ታቦተ ጽዮንነት፥ ኋላም፡ በፍጻሜው የሕይወት ዘመን፡ ድንግል ማርያምን፡ ወደፊት፡ በጊዜው እንደምዋሓዳት፡ ገና፡ በእናቷ በሓና ማሕፀን ሳንፈጥራት ያወቅኋትና የቀደስኋት፥ ከዚያም፡ እንደዚያ፡ አስቀድሜ ባወቅሁትና በቀደስሁት፡ በዚያ ሕያው ሰውነት፡ በማሕፀን እያለሁ፡ ከኢትዮጵያዋ አኵስም ተነሥቼ፡ ወደኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ከተማ፡ ወደኢየሩሳሌም የመመለሴን ተአምራዊ ዜና የገለጠው ማነው?

በዚያም፡ በሊባኖስ ተራራ የመወለዴን፥ በተወለድሁ፡ በሦስት ዓመታቴ፥ ከሦስት ወራቴና ከሦስት ቀናቴም፡ ቀድሞ፡ በጽላተ ኪዳንነትና ታቦተ ጽዮንነት ወደነበርሁባት ቤተ-መቅደስ የመግባቴን፥ በመጨረሻም፡ ልጄን ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ እንደትንቢት ቃላችን፡ በበረት እወልደው ዘንድ፡ ወደቤተ-ልሔም እስክኼድ ድረስ፡ በዚያ፡ በኢየሩሳሌሟ ቤተ-መቅደስ የመቆየቴን እውነተኛ ዝክረ-ነገር፡ ለመላው ፍጥረታተ-ዓለማት፡ በይፋ የዘገበ ማነው? በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችን የኾናችሁት፡ እናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ አይደላችሁምን? አዎን! እናንተ ብቻ ናችሁ! ሌላማ፡ ማን አለ? ማንም የለም።

ይህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም፡ ሰብአዊቷን ድንግል ማርያምን፡ ወደፊት፡ በጊዜው እንደምዋሓዳት፡ ገና፡ በወላጆቿ፡ በሓና ማሕፀን ሳንፈጥራት የማወቄና ሰውነቷን የመቀደሴ ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ ሥራ፡ እውን ኾኖ የታየውና በጊዜው ተፈጽሞ የተገኘው፡ በቀደመው ነቢያችን፡ በኤርምያስ አንደበት፡ ስለራሱ፡- **"ወኮነ ቃለ-እግዚአብሔር ኀቤየ፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር፡- 'ዘእንበለ እፍጥርከ፡ እምከርሠ-እምከ፡ አእመርኩከ፤ ወዘእንበለ ትፃዕ እማሕፀን፡ ቀደስኩከ፤ ወነቢየ ረሰይኩከ፡ ለአሕዛብ።'**

"የእግዚአብሔር ቃል፡ ወደእኔ መጣ፤ እግዚአብሔርም፡ እንዲህ አለኝ፡- 'በእናትህ ማሕፀን ሳልፈጥርህ፡ ዐወቅሁህ [ወደድሁህ]፤ ከእናትህ ማሕፀን ሳትወጣም፡ መረጥሁህ፤ ለአሕዛብም፡ መምህር አደረግሁህ።'" ብለን ባናገርነው የትንቢት ቃል መሠረት እንጂ፡ እንዲያው፡ እንደእንግዳ ደራሽ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ወይም፡ በድንገት የኾነ፡ አጋጣሚ ድርጊት አይደለም። (ኤር. ፩፥ ፬-፭።)

፫ኛ፡ በዚህ ኹሉ በተገለጠው የእግዚአብሔር እውነት፡ እናንተ ልጆቼ፡ **"ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!**

"ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" እያላችሁ፡ በዘወትሩ የኪዳን ጸሎታችሁ፡ በዝማሬ የምታሰሙት፡ ይህ፡ በቀዳሚነት የተፈጸመው፡ የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ **የዓለም መድኃኒትነት፣** እንደዚሁም፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕም፡ ከጠንቀኛው ተቃዋሚው፡ ከዲያብሎስና በእርሱ አበጋዝነት ከሚካኼደው፣ ማብቂያ ካልነበረው የዝንተ-ዓለም ጦርነት፡ በቤዛነት ተጋድሎውና ሞቱ፡ ይህንኑ ባለጋራውን፡ ፈጽሞ ድል አድርጎት፡ **ዘለዓለማዊዉን ሰላም፡ ለፍጥረተ-ዓለማቱ የማስገኘቱና በደሙ የማተሙ ምሥራች፡** የቀረበውና የተገለጠው፥ በጥራትም የተነገረው፡ በማን ነው? በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችን በኾናችሁት፡ በእናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ አይደለምን? አዎን! በእናንተ ብቻ ነው። ሌላማ፡ ማን አለ? ማንም የለም።

ማዳንን በሚመለከት፡ "ደኅንነት" ስለሚለው የቃሉ ትርጉም፡ "መድኅን"፡ ለወንድ ሲኾን፡ "መድኃኒት" ደግሞ፡ ለሴት በመኾኑ፡ እስካኹን፡ "መድኃኒታችን" እየተባለ የተሠራበት፡ ሃይማኖታዊ መልእክት ያለው ዘይቤ፡ ወደእኔ፡ ወደሴቲቱ ሲያመለክታችሁና ሲመራችሁ የኖረ መኾኑን፡ በገሃድና በግዘፍ ያረጋግጥላችኋል። ለወንድ ቢኾን፡ "መድኅናችን" ያስሰኝ ነበርና፤ ይህን እውነታ፡ በዚህ ገጽታውም ልታስተውሉት የሚያስፈልጋችሁ ይኾናል።

፮ኛ፡ እናንተ ልጆቼ፡ በእኔ የዐዋጅ ቃል፡ ለፍጥረታተ-ዓለማቱ፡ ግልጥ ያደረጋችሁት፡ ይህን፡ የእኔን፡ "እግዚአብሔር እም" የመኾኔን መለኮታዊ እውነት፥ ደግሞም፡ ድንግል ማርያምን በተዋሐድሁባት ቅጽበት፡ ዓለሙን ያዳነው መድኃኒትነቴ እውን የመኾኑን፥ ከዚህም ጋር፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀለ-ሞቱ ተጋድሎውና በአማናዊ የትንሣኤው ድል፡ ዘለዓለማዊዉን ሰላም፡ ለፍጥረታተ-ዓለማቱ የማስገኘቱን ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ ትንግርት ብቻ አይደለም።

ነገር ግን፡ አኹንም እንደገና፡ የእኔን፡ የመንበረ ጸባዖት፡ ቅድስት ሥላሴነት እና ኢትዮጵያነት፥ የእግዚአብሔር መንግሥትነትም ጭምር እንጂ። ታዲያ፡ ይህን፡ መለኮታዊ እውነት፡ እንዲህ፡ ለፍጥረተ-ዓለማቱ፡ አጥርቶና አጉልቶ ያቀረበ ማን ነው? በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችን የኾናችሁት፡ እናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ አይደላችሁምን? አዎን! እናንተ ብቻ ናችሁ! ሌላማ፡ ማን አለ? ማንም የለም።

፯ኛ፡ በመጨረሻ፡-

-በመልካችንና ከእኛ እንደአንዳችን አድርገን ስለፈጠርነው፥ ኋላም፡ ለ፫ሺ፫፻ ዓመታት ያማሰነውንና ያስወሰደውን፡ ይህንኑ መለኮታዊ ስጦታችንን፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በኹለንተና መድኃኒትነት፥ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕም፡ በሰላም ተጋዳይነት፡ እንዲህ፡ እኛው፡ ራሳችን፡ መሥዋዕትነትንና ቤዛነትን ከፍለን በማደስና በማስመለስ ስለዋጀነው [ስለቤዠነው]፡ ስለሰብአዊው ፍጡራችን፡ ስለወንዱም ኾነ ስለሴቱ ታላቅ ክብርና ፍጹም መብት፥

-እንዲሁም፡ በሰማያትና በመላዋ ምድር ላይ ሰፍና ስላለችው፡ ስለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በእኛ ዘንድ ያለውን፡ መንፈስ ቅዱሳዊ ዕውቀት፡ በፍላጎታችሁና በፈቃዳችሁ፥ በገዛ ምርጫችሁም ተቀብላችሁ፡ ለየራሳችሁ ብቻ ሳይኾን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ ለማሳወቅ፡ በኪዳናዊ ተልእኳችሁ፡ እንዲህ በታማኝነትና በቆራጥነት ጸንታችሁ የቀጠላችሁ፤

-በዚህ ዓለም፡ በምድር ላይ፡ በአኹኑ ዘመን፡ እንደምታዩትና እንደምትሰሙት፡ ከእናንተ በቀር፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ፥ ዓለማዊና ሃይማኖታዊ የኾነ፡ ሌላ ሰብኣዊ ወገን፥ ወይም፡ ድርጅት፥ ወይም፡ ቤተ-ሕዝብ፥ ወይም፡ ቤተ-ክህነት፥ ወይም፡ ራሱን፡"መንግሥት" ብሎ የሚጠራ ቤተ-ምልክና፡ ከቶ በእነማን ዘንድ፥ ወይም፡ በየትኛው ቦታ አለ? የለም።

ይህን፡ ከእኛ የቀረበላችሁን መለኮታዊ ተልእኮ ለመፈጸም፡ በምድር ላይ፥ በፍጡራን መካከል፡ የተገኛችሁት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችን የኾናችሁት፡ እናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ አይደላችሁምን? አዎን! እናንተ ብቻ ናችሁ! ሌላማ፡ ማን አለ? በማንስ ዘንድ አለ? የትስ አለ? የለም።

## የኢትዮጵያ ልጆች ለመኾን ያበቃችሁ፡ የሙያ መሥፈሪያና የተቀላችሁት በረከት።

እናንተ፡ ይህን የመሰለውን መለኮታዊና ኪዳናዊ የኾነ፡ የእውነተኛነትን ቊም-ነገር ለመከተልና የታማኝነትን ምግባርን ለመፈጸም የቻላችሁት፡ ቀደም ብዬ እንዳልኋችሁ፡ እኛ፡ እናንተን፡ ከመላዎቹ ሰብአት ፍጡሮቻችን መካከል፡ በተለይ፡ ለእናንተ፡ ያደረግንላችሁ፡ አድላዊ ነገር ኖሮ፥ ወይም፡ መርጠናችሁ ሳይኾን፡ እኔ እግዚአብሔር እም የተዋሓድኋት እና የሰው ወገን የኾንሁት እኔ ድንግል ማርያም እንዳደረግሁት ኹሉ፡ እናንተም፡ በእየራሳችሁ ፍላጎትና ምርጫ፡ በፈቃዳችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ ኪዳናዊነት፥ ለተልእኮውም በማብቃታችሁ አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው እንጂ።

ከዚህ፡ የኢትዮጵያዊነት ቅድስና ወጣኒነታችሁ [ጀማሪነታችሁ] የተነሣ፡ በእናንተ መንፈሳዊ አእምሮ ውስጥ፡ በእየጊዜው እየሠረፀ የገባው፡ መንፈስ ቅዱሳዊው የዕውቀት ጸጋችን፡ እያደር እየጨመረና እያደገ፥ እየጠለቀና እየጸና መኼዱን ቀጥሎ፡ እነሆ፡ ዛሬ ካላችሁበት የብቅዓት ደረጃ ሊደርስላችሁ ችሏል። ይህም ጣፋጭ ፍሬያማነታችሁ፡ እኛን፡ እግዚአብሔር አብንና እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፥ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን፡ የቱን ያህል እንዳስደሰተን፡ ራሱ መንፈሳችሁ፡ ለእናንተም፤ ለእኛም አሳውቆናል።

ስለዚህ፡ እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ጸጋና ማዕርግ በማብቃታችሁ፡ እኔም፡ ከእናትነት ፍቅሬና ምርቃቴ ጋር፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ "ኀሸ ልጆቼ!" እያልኋችሁ፡ እየባረክኋችሁና ግንባራችሁን፡ በነፍስ ወከፍ፡ እየሳምኋችሁ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ "**እብለክሙ፤ ከመ ከመዝ፡ ይከውን ፍሥሐ፡ በሰማያት፡ በቅድመ መላእክተ-እግዚአብሔር!**

"እላችኋለሁ፤ በሰማይ፤ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ደስታ ይኾናል!" ያለው ቃሉ፡ ለእናንተ ልጆቻችን፡ ይኸው፡ ያለማቋረጥ እየተፈጸመላችሁ መኾኑን አበሥራችኋለሁ። (ሉቃ. ፲፭፥ ፫-፲።)

በመንፈስ ቅዱሳዊው ዕውቀት እየጐለመሳችሁና እየጐለበታችሁ በምትጓዙበት፡ በዚህ የዕድገት ኺደትና የብልጽግና ይዘት፤ እያሳያችሁን ያለው ጣፋጭ ፍሬያማነታችሁ፡ "በዚህ ጊዜ፥ በዚህ ደረጃ ይቆማል፥ ያበቃል!" ማለት አይደለም፤ እንዲያውም፡ በበለጠ እየጨመረና እያደገ፥ እየጠለቀና እየጸና መኼዱን ይቀጥላል እንጂ፡ አያቆምም፤ አያበቃምም።

የእናንተ፡ ነፍሳችሁ፡ በሥጋዊ አእምሮዋ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በመንፈሳዊው አእምሮዋ ስለምትጠቀም፡ ለሥጋዋ ጭምር የሚበጀውን፡ መልካሙን ኹሉ በማስገኘት፡ ይኸው፡ ለኹለንተናዋና ስለኹለንተናዋ፡ በኹለንተናዋ ብቁ ከመኾን ደርሳለች።

በዚህ ብቅዓታችሁ ምክንያት፡ አኹን የደረሳችሁበትን የህልውናችሁን ደረጃ የሚያሳይዋችሁ፥ የማንነታችሁና የምንነታችሁ መገለጫ፥ የሕይወታችሁም መመሪያ የኾኑት፥ ከዚህ ቀደም ብሎ በወጣው፡ በ፲ (ዐሥረ)ኛው የዐዋጅ ቃሌ ውስጥም ተካትተው የነበሩት፡ አራቱ መደበኛና ቋሚ ጸሎቶቻችሁ፡ ዛሬ፡ ከዚህ የዕውቀት ደረጃችሁ ጋር የሚነጻጸሩ፥ ፍላጎታችሁን የሚያረኩና በመንፈስ ቅዱሳችን የተሟሉ ኾነው፡ ትገለገሉባቸውና ታገለግሉባቸው ዘንድ፡ እነሆ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ እንዲቀርቡላችሁ አድርጌአለሁና፡ ወስዳችሁ ተጠቀሙባቸው።

+ + +

## ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያ።

### ንሕነ፡ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡-

*ነአምን፡ በአሓዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ።*

*ወነአምን፡ በትሥልስተ አሓዱ አምላክ፡ ዘግህደ በተዋሕዶ ህላዌሃ፥ ወበአካላ ለድንግል ማርያም፡ እንተ ይእቲ፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፥ ወኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር።*

*ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልድ ዋሕድ፡ እምእግዚአብሔር አብወእም፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ መሲሕ፥ ብርሃን፡ ዘእምብርሃን፥ አምላክ፡ ዘእምአምላክ፡ ዘበአማን፤ ዘተወልደ፡ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ አብወእም፡ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ፡ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ፡ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ። ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ ሰላምነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ፤ ወተሠገወ፤ ወኮነ፡ ብእሴ ፍጹመ፡ በነሢአ ሥጋ፡ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ፡ እምነፍሳ፡ እምማርያም፡ እምቅድስት ድንግል፡ ዘተዋሓደት እግዚአብሔር አብወእም፡ ለመድኃኒትነ፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ዘበቅድም። በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፤ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ። ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት። ዐርገ በስብሓት፡ ውስተ ሰማያት። ወነበረ፡ በየማነ አቡሁወእሙ፥ በመንበሩ ዘበዕሪና። ዳግመ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኰንን፡ ሕያዋነ፥ ወሙታነ። ወአልባቲ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡ ዘተሰምየት፡ "ኢትዮጵያ"።*

*ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፥ ማኅየዊ ዘበአማን፥ ዘሠረፀ እምእግዚአብሔር አብወእም፥ ዘንሰግድ ሎቱ፥ ወንሰብሖ፡ ምስለ አብወእም፥ ወወልድ፥ ወዘነበበ በነቢያት፥ ዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፥ ወጸጋሁ፡ ዘመልዓ ዓለመ፡ በምሥዋዐ መድኃኒትናሃ፡ ለድንግል ማርያም፥ ወበቤዛ መስቀሉ፡ ለኢየሱስ መሲሕ።*

*ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ ኢየሱስ መሲሕ፡ እምጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብኣት ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት፡ በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሓዋርያት። በውስቴታ፡ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፥ ወምእመናት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ።*

*ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ዘረከብናሃ፡ እምመንፈስ ቅዱስ፥ ወእምእሳት፡ ለስርየተ ኃጢአት።*

*ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ፡ ዘለዓለም። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።*

## ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያ።

### ንሕነ፡ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡-

ነአምን በኢትዮጵያውናን፡ ዘኪዳን ቅዱስ፥ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወሀቦን እግዚአብሔር፡ ለውሉደ ሰብእ።

አምላክነ፡ ሣረረ ዝንቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፥ ወኢትዮጵያዊት፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ እምሥርዓተ ሰብሳብ፡ ዘአዳም፥ ወሔዋን፡ በዘመነ ፍጥረት ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕንፃ፡ በቀስተ ደመናሁ፡ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ፡ ዘመልከ-ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት፡ ዘግህደ በፅምረተ አሥራወ ዘርዖሙ፡ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላዊ፣ ከመ ያስተሰነአዎ ኰለንታሁ፡ በኪዳነ ኦሪት።

ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ፥ ወዘተወልደ እምድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት፡ እምዛቲ ሥርው ምልዕት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ።

በእንተዝ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዘፈት፡ በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፥ ወበሰብእናሃ ለኢትዮጵያዊት፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኀቤሁ፥ ወበኀቤሃ፡ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ።

ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ክርስቲያን"፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ "ክርስቶስ"፡ ነአምን፡ ከመ ውእቱ ኢየሱስ መሲሕ፡ ካህንነ፥ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፤ ወዘኮነ አርአያሁ ለመሲሕ ኢየሱስ፣ በልደቱ ዘኮነ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት።

ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ፡ "ደቂቀ ኢትዮጵያ"፡ በስመ ዚአሃ፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ"፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ድንግል ማርያም፡ ዕፀ ሕይወት፥ ወእመ-ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ-ሰማያት ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለአምላክ።

ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ፡ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶን፡ ሓመልሚለ፥ ወወርቀ፥ ወቀይሓ፡ ዘተውህበ ለነ እምእግዚአብሔር፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም።

ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ እምአምላክነ፡ ወበዘውእቱ ዘተነግረ በእንተ ኢየሱስ መሲሕ፡ መፈጽም ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝንቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፥ ወበቃለ ትንቢት ዘተነግረ፡ በእንተ ድንግል ማርያም፡ እንዘ ይብል፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"።

ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ፥ ወካህናቲሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ፡ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር፡ በመንፈስ፡ እንበይነ ጸጋሁ፡ ዘኪዳኑ ቅዱስ።

ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ፡ እንበለ ፅርዓት፡ ለስርየተ ኃጢአት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።

ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ ይትአወቅ በምግባሪነ፡ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም፡ በተዋሕዶተ ፍቅርነ፡ ለእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።

ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳነ ቅዱስ፡ በልቦናነ፤ ወመሀረነ፤ ወረሰየነ፡ ንዕቀቦ በሀልዎትነ፡ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

## ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡
## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

አ አቡነ፥ ወእምነ፥ ወእኁነ፥ ወእኅትነ፥ ወመንፈስነ እግዚአብሔር! ነአኵተከ እግዚኦ፥ ወንሴብሓከ፤ ንባርከከ እግዚኦ፥ ወንትአምነከ፤ ንገኒ ለከ እግዚኦ፥ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ፤ ንሰግድ ለከ፤ አ ዘለከ! ይሰግድ ኵሉ ብርክ፤ ወለከ ይትቀነይ፡ ኵሉ ልሳን።

አንተ ውእቱ፡ አምላከ አማልክት፤ ወእግዚአ አጋእዝት፤ ወንጉሠ ነገሥት። አምላክ አንተ፡ ለኵሉ ዘሥጋ፤ ወለኵላ ዘነፍስ። ወንጼውዐከ፣ በእንተ ዘተወከፍከ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዘ ይብል፡ "አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡- 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ! ትምጻእ መንግሥትከ! ወይኩን ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፡ ከማሁ በምድር! ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፡ ሀበነ ዮም! ሕድግ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፣ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ! ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት! አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ፡ እምኵሉ እኩይ! እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል፥ ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም።'" ወበእንተ ዘአብዛኅከ ለነ፡ ኂሩትከ፤ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፤ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፤ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ነፍስነ፥ ወሥጋነ።

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ በምክንያተ ምሥዋዐ መድኃኒትነ፡ ዘእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወቤዛ ሰላምነ፡ ዘእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።

በእንተዝ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ በምድር፣ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ። ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ በምድር። ወመጽአት መንግሥትከ። ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፡ ከማሁ፡ ኮነ በምድርኒ።

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኵሉ ሀልዎትነ፤ ወአኮ ሲሳይ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ። ወመጦከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘነሥአ እምእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፣ ዘኮነ ለነ፡ ምግበ ነፍስ፥ ወመድኃኒት፣ ዘይረስየነ ሕያዋን ዘለዓለም፤ ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ወአበሳነ ግሙራ፥ ወዘኢ.ማእዜ፤ ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ።

ወዐልዓልከነ፡ በልደትነ፡ እምጥምቀት፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት፡ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ፤ ወበጸጋከ፡ ዘንስሓ።

ወአውጻእከነ፡ እመንሱት ዘዘዚአሁ፤ ወአድኃንከነ፡ እምኵሉ እኩይ፤ ወሞዕክዎ፡ ለዲያብሎስ፡ አቡሃ ለሓሰት፤ ወአሰሰልከ፡ ለሞት፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አሥለጥከነ፡ ንሄሉ፡ በሕይወተ ትንሣኤከ ቅድስት፥ ወበዓለመ ሰንበትከ ዘለዓለማዊት።

አ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፥ ወምሕረትከ፥ ወፍቅርከ፥ ወጸጋከ፡ ዘአወፈይከነ፡ በዘኢይትከሃል ይትነገር መጠኖሙ፤ ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኵሎ ዘንፈቅድ፡ እንዘ አኮ ዘንሰአለከ።

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ ትኄንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘንግሥትነ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥ ወዘንጉሥነ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፥ ዘተብህለ፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፥ ወንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፡ ከመ ትትረአይ፥ ወትሰፍን በገሃድ፥ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሜርዎሙ፡ ለእከይ፥ ወለኃጢአት፥ ወለሞት። እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት። ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

## ጸሎተ ሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም፡

## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

አ እግዚአብሔር እምነ፥ ወመድኃኒትነ ማርያም! ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ። ድንግል በኅሊናኪ፤ ወድንግል በሥጋኪ። ይደልወኪ ዝ ሱላሜ፣ እስመ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ።

አንቲ ይእቲ ሐዌን ቅድስት፤ ወቡርክት፡ እምኵሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ፡ ዘዕፀ ሕይወት፣ በዘውእቱ ኮነ፡ አዳምሁ ቅዱሰ።

ተፈሥሒ! አ ንግሥትነ፡ በሰማይ፥ ወበምድር! እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፡ እንዘ ይብሉኪ፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥ ወንሕነኒ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "እምነ ጽዮን!"

ንዌድሰኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ አ ምልዕተ ጸጋ!" እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ ድኅነትነ።

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ክመ እምኔነ፡ ማሕፀንተኪ፡ በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፤ እስመ አንቲ ይእቲ፡ እምነ ዘምሕፅና፤ ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡ በቃለ አማሕፅኖ ዘወልድኪ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ አምላክነ፥ ወሰላምነ።

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘተገብረት ለነ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

# <u>ቃለ አሚኖት፡ ዘደቂቀ ኢትዮጵያ</u>



| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር |
| እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ | እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም |
| ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ | እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ |
| ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። | ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ። |

---

አነ_________________________________፥ ወስምየ ዘክርስትና____________________________________፥

ወልደትየ ዘኮነ በወርኃ__________________፥ በ_______ዕለት፥_________________ዓ. ም. በሀገረ ______________________፤ዮም፡ በዝ ወርኃ____________፥ በ_______ዕለት፥___________ዓ. ም.

እቀውም፡ በቅድመ መንበሮሙ ለእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ወለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በአምልኮተ ጽድቅ ዘመንፈስ ቅዱስ፡ ወናሁ አሰምዕ ስምዕየ በአጽንዖት፤ እንዘ እብል፡-

"አነ ውእቱ ኢትዮጵያዊ/ት ዘኪዳን ቅዱስ፡ ዘእሄሉ፡ በዐቂበ ርትዕት ሃይማኖትየ፡ ጽሪት፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ እንተ ተመሥረት፡ በዝንቱ ኪዳን ቅዱስ፡ ዘውእቱ መዝገቦሙ ለሰብዓቱ ኪዳናት፡ ዘተካየዱን እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ፤ እላንቱ፡ ዘተወጥና በአዳም ወሔዋን፥ ወተሓደሳ በሰብእናሆሙ ለኖኅ፥ ወለመልከ ጼዴቅ፥ ወለአብርሃም፥ ወለሙሴ፥ ወለዳዊት፡ እስከልደተ ኢየሱስ መሲሕ እምድንግል ማርያም፡ ዘተፈጸማ በዛቲ ትስብእት፥ ወዘተግህደት በምግባርየ፥ ወዓዲ ዘእሄሉ በአንጽሖተ ርእስየ፡ በንስሓ፥ ወበአጽድቆተ ሰብእናየ፡ በተመጥዎተ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ።

"ኦ እግዝእትየ ወመድኃኒትየ፥ ሃይማኖትየ ወሀገርየ፥ እምየ ወንግሥትየ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም! አበርክ ቅድመ መንበርኪ ወአቀርብ ለኪ፡ አምኃየ ዘስባሔ፡ በቃለ ገብርኤል መልአክ ቅዱስ፡ እስመ በፍቅርኪ ወበረድኤትኪ፡ ኮንክኒ ማሕፀንትየ፡ ከመ እጽናዕ በኢትዮጵያውናየ ዘቅዱስ ኪዳን፡ በኵሉ መዋዕልየ።"

"ኦ እግዚእየ ወሰላምየ፥ ካህንየ ወንጉሥየ ኢየሱስ መሲሕ! እሰግድ በቅድመ መንበርከ ወእሴብሓከ፡ እስመ አብቍዐተኒ ከመ በክሡት አሰምዕ፡ ዝ ስምዕ፡ በተአምኖትየ ዘቃልከ መለኮታዊት፡ ዘትብል፡ 'ኵሉ ዘየአምን ብየ፡ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ አአምኖ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት፤ ወዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ እክሕዶ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት።' አሜን።" (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

# የኢትዮጵያ: የሃይማኖት ጸሎት።

## እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡-

ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብወእም እናምናለን።

መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በድንግል ማርያም፡ የተዋሕዶ አኗኗርና አካል በተገለጠው፡ በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የእግዚአብሔር አብወእም ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ፡ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብወእም ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ፡ በእርሱ የኾነው፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ ስለሰላማችን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ ስለመዳናችን ከተዋሓዷት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱና እናቱም ቀኝ፡ በእኩያ ዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። "ኢትዮጵያ" ለተባለችው መንግሥቱም፡ ፍጻሜ የላትም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከእግዚአብሔር አብወእም የሠረፀና በነቢያት ዐድሮ የተናገረው፥ በሓዋርያት ላይ የወረደውና በድንግል ማርያም፡ የማዳኗ ምሥዋዕነት፥ በኢየሱስ መሲሕ፡ የመስቀሉ ቤዛነትም፡ ዓለሙን፡ በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብወእም እና ከወልድ ጋር እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሓዋርያት ጉባኤ በፈጸማት፥ ካህናት፡ ከእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውን፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባት፥ ምእመናንና ምእመናትም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን።

ኃጢአት በሚሰረይባት፥ ከመንፈስ ቅዱስና በእሳት በተቀበልናት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

# <u>የኢትዮጵያ፡ የቃል ኪዳን ጸሎት።</u>

## እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡-

እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን የኢትዮጵያዊ፥ የኢትዮጵያዊት ሰውነት፡ **በመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን፡** በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤ ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቍርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ **በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤

**በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእርሷ በነሣው ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።

ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው እና ኢትዮጵያዊቷ ሰውነት ገዝፋ፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋንም፡ በምሥጢረ-ተዋሕዶ፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን፡ "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በቀደመው ዘመን፡ ለእርሱ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕይወት ዛፍ፥ የሕያዋን እናትና፥ ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

በአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ኅብረ-ቀለማት ያሸበረቀው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ መሲሕ የተነገረው፡ "**የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!**" የሚለው መለኮታዊ ቃል እና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "**ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታቀርባለች!**" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን።

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን፡ ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢኣታችንን፡ ዘወትር በንስሓ እያጠራንና ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋና ደም እየተቀበልን፡ መኖር እንዳለብን እናምናለን።

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ ለእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ባለን የተዋሓደ ፍቅር ኾነን፡ በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት።

አባታችንና እናታችን፥ ወንድማችንና እኅታችን፥ መንፈሳችንም፡ እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን፤ አቤቱ እናወድስሃለን፤ እንቀድስሃለን፤ አቤቱ እንታመንብሃለን፤ እናገንንሃለንም፤ ጒልበት ኹሉ፡ ለአንተ ይሰግዳል፤ አንደበትም ኹሉ፡ ወደአንተ ይጮሃል። አንተ፡ የአማልክት አምላክ ነህ፤የገዢዎች ገዢ ነህ፤ የንጉሦችም ንጉሥ ነህ። አንተ፡ የሥጋዊው ኹሉ፥ የነፍሳዊዉም ኹሉ ወገን ፈጣሪ ነህ።

**"እናንተ ስትጸልዩ፡ 'የሰማዩ አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ!መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ በሰማይ እንደኾነ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ይኹን! የየዕለቱን ምግባችንን፡ ስጠን ለዛሬ! ኃጢኣታችንንና በደላችንን፡ ይቅር በለን! እኛም የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል! አቤቱ ወደፈተና አታግባን! ከክፉው ኹሉ፡ አድነን እንጂ! መንግሥት፡ የአንተ ናትና፥ ኃይልና ምስጋናም፤ ለዘለዓለሙ።' በሉ!"** ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ መሲሕ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ፡ ይኸው አኹን እኛም፡ እንደዚሁ፡ ስምህን እየጠራን፡ እናመሰግንሃለን።

በእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የመዳናችን ምሥዋዕነት እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የሰላማችን ቤዛነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን። ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም፡ የምትኖር ኾንህ። ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ። መንግሥትህም መጣችልን።
በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ፡ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን። ለዘለዓለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንንም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ከእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውን፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢኣታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም፡ የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የተቀበልነውን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን።

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ የሓሰቱን አባት ዲያብሎስንም፡ ድል አድርገህ፥ ሞትንም አስወግደህ፡ በተቀደሰችው የትንሣኤህ ሕይወትና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም ለመኖር አበቃኸን።

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም፡ የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ታደርሳለች!" በተባለችው፡ በእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ንግሥትነት እና "የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!" በተባለው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ንጉሥነት የምትመራው፥ እኛ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፉትን፥ ኃጢኣትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን።

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ የአንተ ናቸው፤ ዛሬም፣ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት።

እግዚአብሔር እናታችንና መድኃኒታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን። በአሳብሽ፡ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም፡ ድንግል ነሽ። በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ይህ ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል።

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ።

ቀድሞ በነቢያት፡ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!" የተባልሽ፥ እኛም፡ "እናታችን ጽዮን!" ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ!

እግዚአብሔር፡ አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን፡ ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ "ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ!" እያልን፡ ዘወትር እናወድሻለን።

በአምላካችንና በሰላማችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ አንቺ፡ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም፡ ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም፡ እንደማይለየን እናምናለን። ይህን ያደረገ ቸሩ አባታችን ልዑል እግዚአብሔርን፡ እናመሰግነዋለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

# የኢትዮጵያ ልጆች፡ የታማኝነት ማረጋገጫ ቃል



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ፣
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፣
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዚአብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

እኔ፡ ______________________ ፥ በክርስትና ስሜ ______________________ የተባልሁ፥
በ ______________ ቀን፥ ____________ ዓ. ም. በ ______________________ የተወለድሁ፡
ዛሬ፡ በዚህ በ ______________ ቀን፥ ____________ ዓ. ም. በእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ መንበር ፊት፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ቆሜ፡ እንዲህ እያልሁ፡ የምስክርነት ቃሌን በማረጋገጥ እሰጣለሁ።

“እኔ፡ በኢትዮጵያ የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች ውስጥ እንደተገለጸው፡ በአዳምና ሔዋን ተጀምሮ፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት በኩል እየታደሱ፡ እስከኢየሱስ መሲሕና ድንግል ማርያም ደርሶ በተፈጸመው፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉትን፡ ሰባቱን ኪዳናት በአጠቃለለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተመሥርታ የቆመችውን፥ በምሥጢረ ተዋሕዶ የጠራችውንና የቀናችውን ሃይማኖቴን ጠብቄና በምግባር አጽንቼ፡ ራሴን፡በንሥሓና በሥጋ ወደሙ እያጸደቅሁ የምኖር፡ **የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ/ት ነኝ።**

“እግዚአብሔራዊት እመቤቴና መድኃኒቴ፥ ሃይማኖቴና አገሬ፥ እናቴና ንግሥቴ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ጸንቼ እኖር ዘንድ፡ በፍቅርሽና በረድኤትሽ ስላልተለየሽኝ፡ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ በመንበርሽ ፊት ሰግጄ፡ የምስጋና ሰላምታዬን አቀርብልሻለሁ።

“አምላኬና ሰላሜ፥ ካህኔና ንጉሤ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ!"**በሰው ፊት፡ በእኔ አምኖ ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ።"** ያልከውን መለኮታዊ ቃልህን አምኜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን የምስክርነት ቃል፡ በይፋ እንድሰጥ ስላበቃኸኝ፡ በመንበርህ ፊት እየሰገድሁ አመሰግንሃለሁ። አሜን።" (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

ተዐውደ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፭ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ \+ \+